# የትንሳኤ ሬዲዮ

## የኢትዮጵያ ህዝብ ልሳን ሆና ትቀጥል ዘንድ ህዝባዊ ድጋፍ ትሻለች !

ማርች 26፣ 2007

**ሕዝባችን** በረጂም ጊዜ ታሪኩ የእራሱን መጻኢ የፖለቲካ እድል በእራሱ ለመወሰን ከፍተኛ ትንቅን ቅ ላይ እንዳለ በግልጽ ይታወቃል:: በዚህ እልክ አስጨራሽ የነጻነት ትግል ትንሳኤ ኢትዮጵያ ድምጽ አልባ ለሆነው ድምጽ በመሆን አማራጭ የመረጃ ምንጭና የለውጥ ማእበሉ ተዋናይ በመሆን ታሪካዊ ሚናዋን እየተጫወተች ትገኛለች:: ትንሳኤ ሬዲዮ የኢትዮጵያንና አካባቢውን አገሮች በመሸፈን የወያኔ/ኢህአዴግን የመረጃ ሞኖፖል ሰብራ የበረከትንና የዋርድያዎቹን የመረጃ አፈና ሰንሰለትን በጣጥሳ የህዝባችንን የአልገዛም ስሜት በማጠናከር የለውጥ እስትንፋስ ለመሆን በቅታለች:: በመላው አለም ተበትኖ የሚገኘውም ኢትዮጵያዊ ስለ አገሩ መረጃ በማግኘት እንደ አንድ ህዝብ በመንፈስ እንዲገናኝና በአገር ውስጥ ካለው የለውጥ ሃይል ጋር እንዲተባበር፥ ለህዝባችን ነጻነትና ለአገራችን ብሄራዊ ክብር በጋራ ዘብ ይቆም ዘንድ በድህረ ገጿ የማይናቅ አስተዋጽኦ እያበረከተች ትገኛለች::

**ትንሳኤ** ኢትዮጵያ ሬዲዮ በጥቂት አገር ወዳዶች ያላሰለሰ ጥረት ተመስርታ የወያኔ/ኢህአዴግ ዘረኛ አምባገነኖች የጥላቻ ፖለቲካን አጥብቃ እየታገለችና እያጋለጠች የኢትጵያዊነት የጋራ አገራዊ መንፈስና ስነልቦና እንዲጠበቅ፥ ለኢትዮጵያውያን ሁሉ የአንድነት፥የዴሞክራሲና የነጻነት ድምጽ በመሆን እነሆ ሁለተኛ ዓመትዋን ለማክበር በዝግጅት ላይ ትገኛለች:: ይሄንን የልደት በዓልዋን በታላቅ ድምቀትና በልዩ ልዩ ዝግጅት ለማክበር ያገልግሎትዋ ተጠቃሚዎች ህልውናዋንና አገልግሎትዋን ለማቆየት የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ድጋፍና ትብብር ትሻለች ትንሳኤ ኢትዮጵያ ለአገርና ለወገን የገባችውን ቃልኪዳን ጠብቃ የመረጃ አቅርቦቷን እንድትቀጥል ማስቻል፥ ህልውናዋን መጠበቅና አገልግሎቷን ማጎልበት በእያንዳንዱ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ትከሻ ላይ የወደቀ ታላቅ ሀላፊነት ነው::

ትንሳኤ ሬዲዮ የተመሰረተበትን ሁለተኛ አመት ምክንያት በማድረግ ለመላው ኢትዮጵያዊያን የሚከተሉትን ጥሪዎች ያቀርባል።

## 1ኛ - ለመላው ኢትዮጵያዊያን

ድምጽ ለሌለው ኢትዮጵያዊ ድምጽ ለመሆን የቻልነው በናንተ እርዳታ በመሆኑ፤ አሁንም ይኸው እርዳታችሁ ተጠናክሮ እንዲቀጥል በድጋሚ ጥሪ እናደርጋለን።
ትንሳኤ ኢትዮጵያ ሬዲዮ ይበልጥ ተጠናክራ ሃምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ ለሃምሳ ሰው ጌጡ ነው እንዲሉ ከጥቂት አገር ወዳዶች ሸክምነት ወደ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ የጋራ ጌጥነት ትሸጋገር ዘንድ የገንዘብ እርዳታችሁንና ሁለንተናዊ ድጋፋችሁን ዛሬ ትሻለች:: ዛሬ በመላው አገራችን ገጠርና ከተማ በአጭር ሞገድ፥ በድረ ገጿ በመላው አለም አገልግሎትዋን በመስጠት ታላቅ ህዝባዊ አመኔታንና ፍቅርን ያተረፈችው ትንሳኤ ኢትዮጵያ ሬዲዮ ትቀጥል ዘንድ ሳይውሉ ሳያድሩ ድጋፍዎን ያበረክቱላት ዘንድ በአክብሮት እንጠይቃለን ::

የሕዝባችን አማራጭ የመረጃ ምንጭ እንዳይደርቅ የሚቻለንን ድጋፍ በመስጠት ትንሳኤ ኢትዮጵያ ሬዲዮ እስከ ኢትዮጵያ ትንሳኤ ትቀጥል ዘንድ 1ኛ / በየአካባቢያችሁ የትንሳኤ ወዳጆች ከለብን በማቋቋም ቀጣይ የሆነ እርዳታና ድጋፍን በማስተባበር 2ኛ/ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚችለውን

የገንዘብና የማቴሪያል ድጋፍ በ ትንሳኤ ድረ ገጽ (Tensae.Net) በሰፈሩት የእርዳታና ድጋፍ መስጪያ መንገዶችና  የእርዳታ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች በመጠቀምና በቀጥታ በትንሳኤ የባንክ ሂሳብ Tensae Ethiopia Inc. Account Number 2000024524078 Thirteen numbers , Routing Number 054001220 Nine numbers It is at Wachovia Bank, in Washington DC. ገቢ በማድረግ ወይም ቼኮቻችሁን በሚከተለው አድራሻ You can mail the check to the following address: Tensae Ethiopia Inc. c/o P.O. Box 2945 Washington, DC 20013-2945

በመላክ ለአስቸኳይ ጥሪያችን ወገናዊ ምላሽ ትሰጡ ዘንድ የአክብሮት ጥሪያችንን እናቀርባለን !

## 2ኛ - በውጪ ለምትገኙ ጋዜጠኞች

በውጭ አገር የምትገኙና ለአገራችሁና ለወገናችሁ ሁሉ አስፈላጊውን ሁሉ ስታደርጉ የቆያችሁ ወገኖቻችን፣ በየጊዜው በባህር ማዶ የምታስተላልፏቸው ስራዎቻችሁ የጋን መብራት ሆነው እንዳይቀሩ፣ በውጭ አገር ለሚገኙ ኢትዮጵያዊያዊያን የምታቀርቡትን የሬዲዮ ዝግጅት ወደ ኢትዮጵያም ለማስተላለፍ የሚቻልበትን ዘዴ አዘጋጅተናል። በመሆኑም ይህን ተፈጻሚ ለማድረግ የናንተን ትብብር እንሻለን፣ ለዚህም በምናዘጋጀው የጋራ መድረክ ላይ ተሳታፊ ትሆኑ ዘንድ ከወዲሁ ጥሪ እናቀርባለን።

## 3ኛ - በውጭ አገር ለምገኙ ኢትዮጵያዊያን

የትንሳኤ ሬዲዮ የህዝብ ድምጽ እንደመሆኑ መጠን በናንተ በኩል ወደ አገር ቤት የሚተላለፈው መልእክት አስፈላጊ መሆኑን እናምናለን። በመሆኑም በቀጥታ ወደ ኢትዮጵያ በምናስተላልፈው የሬዲዮ ዝግጅት ላይ በመሳተፍ አነቃቂ የሆኑ መልእክቶቻችሁን በቀጥታ ማስተላለፍ እንጀምራለን። በመሆኑም የናንተን ተሳትፎ ከምንጊዜውም በላይ እንፈልገዋለን፣ ተሳተፉ።

ለህዝብ ወገኖች ሁሉ የምናስተላልፈው መልእክት ትንሳኤ ኢትዮጵያ ሬዲዮ የሁሉም ኢትዮጵያዊ የጋራ ሀብት ናት:: ለእድገቷና ለምትሰጠው አገልግሎት የሙያ÷ የምክር÷ የተሞክሮና ተግሳጽን ትሻለች:: ለአገልግሎታችን መጠናከር  ሙያ ያለው በሙያው ÷ጉልበት ያለው በጉልበቱ÷ ትርፍ ጊዜ ያለው ጊዜውን በመሰዋት÷ ኢንፎርሜሽን ያለው መረጃን በማቀበል እንዲተባበረን በታላቅ አክብሮት ጥሪ እናደርጋለን:: በዚህ አጋጣሚ በዚህ ታሪካዊ ወቅት ትንሳኤ ኢትዮጵያ ሬዲዮ ጠንካራ የመረጃ ምንጭ ሆና እንድትቀጥል የፋይናንስ ድጋፋችሁ ÷ የቁሳቁስ ና የመረጃ አቅርቦታችሁ÷ ምክራችሁና የሙያ ድጋፋችሁ ላልተለየን ውድ ወገኖቻችን ታላቅ ምስጋና በኢትዮጵያ ህዝብ ስም እናቀርባለን::

በመጨረሻም የትንሳኤ ሬዲዮ የህዝብ ድምጽ በመሆኑ፣ በስራችን ሁሉ ከጎናችን እንድትቆሙ፣ ለአላማችንም መሳካት አብራችሁን እንድትሰሩ ኢትዮጵያዊ መልዕክታችንን ስናቀርብ በታላቅ ደስታ ነው።

የትንሳኤ ሬዲዮ ኢዲቶሪያል ቦርድ ክፍል